ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ የለም ሙሐመድም የአላህ መልክተኛ ናቸው ብለው እስኪመሰክሩ፣ ሶላትን ቀጥ አድርገው እስኪሰግዱና ዘካን እስኪሰጡ ድረስ ሰዎችን እንድጋደል ታዝዣለሁ።

ከኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና
ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ "ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ የለም ሙሐመድም የአላህ መልክተኛ ናቸው ብለው እስኪመሰክሩ፣ ሶላትን ቀጥ አድርገው እስኪሰግዱና ዘካን እስኪሰጡ ድረስ ሰዎችን እንድጋደል ታዝዣለሁ። ይህንን ከፈፀሙ በኢስላም
ሐቅ ካልሆነ በቀር ደማቸውና ገንዘባቸውን ከኔ ጠብቀዋል። ሒሳባቸውም አላህ ዘንድ ነው።" [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

አጋርያን ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ እንደሌለ ብቸኛና አጋር እንደሌለው እስኪመሰክሩ፤ በሙሐመድም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) መልክተኝነት እስኪመሰክሩና ይህ የምስክር ቃል በሚያስፈርደው ነገሮች እስከሚተገብሩ ለምሳሌ በቀንና ምሽት ውስጥ አምስት ሶላቶችን መስገድ ላይ በመጠባበቅ፣ ግዴታ የሆነውን ዘካ ለሚገባው እስኪሰጡ ድረስ አላህ አጋርያንን እንዲጋደሉ እንዳዘዛቸው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ተናገሩ። እነዚህን ጉዳዮች የሰሩ ጊዜ ኢስላም ደማቸውንና ገንዘባቸውን ይጠብቅላቸዋል። በኢስላም ህግጋት መሰረት ለግድያ የሚያበቃቸውን ወንጀል ወይም ጉዳት እስካልፈፀሙ ድረስም እነርሱን መግደል አይፈቀድም። ከዚያም እነርሱን መተሳሰቡን የትንሳኤ ቀን ውስጣቸውን በሚያውቀው አላህ ቁጥጥር ይሆናል።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/4211